Park Hill School District
Building Successful Futures • Each Student • Every Day

# የመድሐኒት አጠቃቀም መመሪያ እና የፍቃድ ቅጽ

**<u>በትምህርት ቤት ለተማሪዎች የሚሰጥ መድሐኒት</u>**

በትምህርት ሰአት መድሐኒት ለተማሪዎች የሚሰጠው እጅግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ከትምህርት ሰአት በፊት እና በኋላ ዶዞች እንዲሰጥ የሚያስችል ጊዜ ሰሌዳን እናበረታታለን፡፡ ይህን ማድረግ ካልተቻለ ቀጥሎ በተቀመጠው ጊዜ ሰሌዳ የህክምና ባለሙያዎች ለልጅዎ በትምህርት ቤት መድሐኒት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ከትምህርት ቤት ነርስ ውጪ የሆኑ ግለሰቦች መድሐኒት ለልጅዎ የሚሰጡበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል(በመስክ ጉዞ በምሳ ሰአታት ወዘተ)፡፡ እነዚህ ሰራተኞች ስልጠና ያገኙ እና በነርስ መመሪያ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡e

**<u>የመድሐኒት አጠቃቀም</u>**

1. በትምህረት ቤት ቆይታ ለተማሪዎች ለሚሰጡ ሁሉም መድሐኒቶች የመድሐኒት ፈቃድ ቅጽ መሙላት እና በወላጅ/አሳዳጊ ሊፈረም ይገባል፡፡ **<u>የአገልግሎት ጊዜው ያበቃ መድሐኒት አይሰጥም</u>**

2. በሀኪም ትእዛዝ የሚወሰዱ ሁሉም መድሐኒቶች ላይ በሀኪም/ፋርማሲስት የተጻፈው አወሳሰድ የሚገልጽ ጽሁፍ ሊለጠፍበት ይገባል፡፡ ይህም በትምህርት ቤት የሚወሰድ ኢንሄለርን ይጨምራል፡፡ ጽሁፉ በኢንሄለር ላይ ሊለጠፍ ይገባል ወይም ኢንሄለሩ ከእነ ማሸጊያው ይዞ ወደ ትምህርት ቤት መምጣት ይገባል፡፡

3. ማናቸውም ያለ ሀኪም ማዘዣ የሚወሰዱ መድሐኒቶች በኦሪጅናል ማሸጊያቸው ሆነው መላክ ይኖርባቸዋል፡፡
   - የህጻኑ ስም በማሸጊያዊ ላይ መጻፍ አለበት
   - **የህክምና ባለሙያው በአዲስ መልክ የመድሐኒት አወሳሰድ መንገድን በጽሁፍ እስካልገለጸ ድረስ መጀመሪያ በማሸጊያው ላይ የታተመው የአወሳሰድ ሁኔታ ብቻ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡**

4. በመድሐኒት አወሳሰድ ወይም ዶዝ ላይ የሚደረግ **<u>ማንኛውም</u>** በሚኖርበት ወቅት ይህንኑ ገልጾ ሀኪም ወይም ፋርማሲስት የሚያቀርበው ፈቃድ ከመድሐኒቱ ጋር አብራ ማያያዝ ተገቢነት አለው፡፡

5. የሚመከረው አካሄድ "እንደ አስፈላጊነቱ" በሀኪም ትእዛዝ የሚወሰድ መድሐኒት ቢበዛ የአንድ ሳምንት ወይም ያነሰ ጊዜ ዶዝ ብቻ ይዞ መምጣት ይገባል፡፡ በየ እለቱ የሚወሰዱ መድሐኒቶች እስከ ሰላሳ (30) ቀናት ድረስ የሚያገለግሉ መድሐኒቶችን ተቀብሎ ማስተናገድ ይቻላል፡፡

6. የጤና ባለሙያዎች ከተማሪ ወላጆች እና መምህራን ጋር በመተባበር ተማሪዎች ወደ ህክምና ጽህፈት ቤት በመምጣት በመደበኛነት መድሐኒት እንዲወስዱ ያበረታታሉ፡፡

7. በሐኪም ክትትል የሚደረግለት ተማሪ በእራሱ የአስም ወይም አለርጅ መድሐኒት መጠቀም የሚችል በሚሆንበት ወቅት የተማሪው ወላጅ ወይም አሳዳጊ ከህክምና ባለሙያ (ነርስ) ጋር በመነጋገር ከህክምና ተቋም በፊርማ አረጋግጦ የሰጠውን ፈቃድ የተሰጠበት ሰነድ እና የመድሐኒት አጠቃቀም እቅድ እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡

8. ***መድሐኒቶች ከተማሪ ጋር በባስ መላች አይፈቀድም፡፡*** ወላጆች/አሳዳጊዎች መድሐኒቶችን ወደ ህክምና ጽህፈት ቤት ሊያመጡ ይገባል፣ ቀሪውን መድሐኒት በሽታው ሲድን ወይም በአመቱ መጨረሻ መጥተው መረከብ አለባቸው፡፡

9. የፓርክ ሂል ስኩል ዲስትሪክት ለተማሪዎች መድሐኒት አያቀርብም፡፡ እነዚህም መድሐኒቶች እንደ አስፕሪን፣ ታይላኖል፣ የሳል ሽሮፕ፣ የሆድ መድሐኒት፣ ሰን ስክሪን እና አንቲ አሲድ ናቸው፡፡

| | |
|---|---|
| የተማሪ ስም፡ | የመድሐኒት ስም: |
| ዶዝ: | በት/ቤት መድሐኒት መውሰጃ ሰአት: |
| መድሐኒት የሚወሰድበት ምክንያት/ሁኔታ: | |
| ልዩ መመሪያዎች: | |

***ከላይ የጠመለከተውን የመድሐኒት አወሳሰድ መመሪያ አንብቤ ተገንዝቤያለሁ፡፡ ከትምህርት ዘመኑ መጨረሻ በፊት የቀሩ መድሐኒቶችን እረከባለሁ ወይም በፓርክ ሂል ፖሊሲ እና አሰራር መሰረት እንዲወገድ ይደረጋል፡፡***

የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ:______________________________ ቀን:____________________